## በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
## የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት

የሠ/መ/ቁጥር 248331

ጥር 30 ቀን 2016 ዓ/ም

**ዳኞች ፡-** ብርሃኑ አመነዉ

በዕዉቀት በላይ

ቀነዓ ቂጣታ

ብርሃኑ መንግሥቱ

ማርታ ተካ

**አመልካቾች ፡-** 1. አቶ አስፋዉ ጋቸና } ጠበቃ ቶሎሳ ደሜ - ቀረቡ

2. አዳነች ባልቻ

**ተጠሪ ፡-** ወ/ሮ አምሳል ታደሰ

መዝገቡ ለዛሬ የተቀጠረዉ መርምሮ ተገቢዉን ትእዛዝ ለመስጠት በመሆኑ ተመርምሮ ተከታዩ ዉሳኔ ተሰጥቷል፡፡

## <u>ዉሳኔ</u>

የሰበር አቤቱታ የቀረበዉ የኦሮሚያ ብሔራዊ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት የከተማ ባለይዞታነት መብት በመፋለም የቀረበ ክስ በይርጋ ቀሪ የሚሆን ነዉ በማለት የይርጋ ጊዜዉ የሚቆጠርበት ጊዜ ተጣርቶ

ማስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ

ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም !

እንዲወሰን ጉዳዩን ለወረዳ ፍርድ ቤት በመመለሱ መሰረታዊ የሕግ ስህተት ተፈጽሟል በሚል ለማሳረም የቀረበ የሰበር አቤቱታ ተከትሎ የተደረገ ክርክር የሚመለከት ነዉ፡፡

ጉዳዩ የተጀመረዉ በአዳማ ወረዳ ፍርድ ቤት ሲሆን የአሁን አመልካቾች በተጠሪ ላይ በመሰረቱት ክስ በአዳማ ከተማ ደጋጋ ቀበሌ ዉስጥ አመልካቾች እንደቅደምተከተላቸዉ በቀን 18/11/1994ዓ/ም በሊዝ የተሰጣቸዉ በካርታ ቁጥር 4655/94 የተመዘገበ 375 ካሬ ሜትር እና በካርታ 4656/94 የተመዘገበ 375 ካሬ ሜትር የመኖሪያ የከተማ ቦታ እንዳላቸዉ ነገር ግን ተጠሪ ከከጎን ያለዉን 1500 ካሬ ሜትር መግዛታቸዉን ምክንያት በማድረግ የአመልካቾችን ይዞታ በሕገ-ወጥ መንገድ በመቀላቀል እንደያዙባቸዉ በመግለጽ እንዲለቁላቸዉ እንዲወሰን ዳኝነት ጠይቀዋል፡፡

ተጠሪ ባቀረቡት የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ መሬቱ ላይ ያለዉን ቤት በሽያጭ ያስተላለፉላቸዉ አቶ ቡልቻ በዳዳ በቀን 01/12/1998ዓ/ም በጨረታ የገዙት እንደሆነ፣ በካርታ ቁጥር 8497/2001 የይዞታ ካርታ በአንድ ግቢ ዉስጥ የሚገኝ 1500 ካሬ ሜትር ቦታ እንደሆነ እና ከ12 ዓመት ከ2 ወር በኋላ በቀን 24/07/2010ዓ/ም በተደረገ የሽያጭ ዉል መግዛታቸዉን በመግለጽ በፍ/ብ/ሕግ ቁጥር 1845 መሰረት ክሱ በይርጋ የታገደ ነዉ በሚል የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ አቅርበዋል፡፡

የወረዳዉ ፍርድ ቤት በመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያዉን አስመልክቶ በሰጠዉ ዉሳኔ ክሱ በይርጋ ቀሪ የሆነ ነዉ በማለት ወስኗል፡፡ ጉዳዩ በየደረጃዉ ባሉት የክልሉ ፍርድ ቤቶች በይግባኝ ታይቶ በመጨረሻም በክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ታይቶ በተሰጠ ዉሳኔ አመልካቾች በተጠሪ ላይ ክስ የመሰረቱት ተጠሪ በ2010ዓ/ም በተደረገ ዉል በአጎራባች ያለዉን ይዞታ መግዛታቸዉን ምክንያት በማድረግ ይዞታችንን ቀላቅለዉ ይዘዉብናል በሚል ምክንያት በመሆኑ ከዚህ ጊዜ ጀምሮ ክሱ እስከቀረበበት ቀን ድረስ ያለዉ ጊዜ ሰባት ወር በመሆኑ በሰባት ወር የሚገደብ የይርጋ ጊዜ የለም በማለት የፍ/ብ/ሕግ ቁጥር 1149/2ን በመጥቀስ የስር ፍርድ ቤቶችን ዉሳኔ በመሻር የወረዳዉ ፍርድ ቤት በፍሬ ነገሩ ላይ አከራክሮ እንዲወስን ጉዳዩን ለወረዳ ፍርድ ቤት መልሷል፡፡

በመቀጠል ተጠሪ ለፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት የሰበር አቤቱታ አቅርበዉ ችሎቱም ግራ ቀኙን አከራክሮ በመ/ቁጥር 221409 በቀን 28/03/2015 ዓ/ም በሰጠዉ ዉሳኔ አመልካቾች ክሱን የመሰረቱት ተጠሪ ይዞታቸዉን ቀላቅለዉ እንደያዙባቸዉ በመግለጽ እንጂ በጉልበት ወይም በሁከት ተግባር ንብረታቸዉን እንደወሰዱባቸዉ በመግለጽ ባለመሆኑ በፍ/ብ/ሕግ ቁጥር 1149/2 ስር የተደነገገዉ የይርጋ ጊዜ ለጉዳዩ ተፈጻሚነት የለዉም፡፡ስለሆነም የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት የዘጋዉን መዝገብ በማንቀሳቀስ የስር ፍርድ ቤቶች የአመልካቾች ክስ በፍ/ብ/ሕግ ቁጥር 1845 መሰረት በአስር ዓመት ይርጋ ጊዜ ቀሪ ይሆናል በሚል በሰጠዉ ዉሳኔ ላይ መሰረታዊ የሕግ ስህተት መፈጸም አለመፈጸሙን መርምሮ እንዲወስን ጉዳዩን መልሶለታል፡፡

ማስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ

ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም !

ከላይ በተመለከተዉ መሰረት ጉዳዩ የተመለሰለት የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት መ/ቁጥር 377349 የሆነዉን መዝገብ በማንቀሳቀስ በቀን 12/07/2015 ዓ/ም በአብላጫ ድምጽ በሰጠዉ ዉሳኔ ክሱ የከተማ መሬት አጠቃቀምን የሚመለከት በመሆኑ፤የከተማ መሬት ደግሞ ንብረትነቱ የመንግሥት በመሆኑ፤እንዲህ አይነት ክስ ለማቅረብ በግልጽ በሕግ የተደነገገወ የይርጋ ጊዜ ባለመኖሩ በፍ/ብ/ሕግ ቁጥር 1677/2 መሰረት የይርጋ ጊዜዉ በፍ/ብ/ሕግ ቁጥር 1845 መሰረት አስር ዓመት ይሆናል፡፡ስለሆነም የወረዳዉ ፍርድ ቤት ለክርክሩ መነሻ የሆነዉ ይዞታ ከአመልካቾች እጅ የወጣዉ ከ1998ዓ/ም ጀምሮ ነዉ ወይስ በ2010ዓ/ም ጀምሮ የሚለዉን የወረዳዉ ፍርድ ቤት በማስረጃ አጣርቶ የአመልካቾች ክስ በይርጋ የታገደ መሆን አለመሆኑን በተመለከተ ዉሳኔ እንዲሰጥ ጉዳዩን ለወረዳ ፍርድ ቤት መልሷል፡፡የልዩነት ሀሳብ ያሰፈሩት ዳኛ ደግሞ ክሱ የባለቤትነት መብት መፋለምን (petitory action) የሚመለከት በመሆኑ በሰ/መ/ቁጥር 43600 ላይ በተሰጠዉ አስገዳጅ የሕግ ትርጉም መሰረት ክስ የማቅረብ መብት በይርጋ የሚገደብ አይደለም ተብሎ ዉሳኔ ሊሰጥ ይገባል በማለት በሀሳብ ተለይተዋል፡፡

አመልካቾች በቀን 07/10/2015ዓ/ም የተጻፈ የሰበር አቤቱታ ያቀረቡት፡-መሬቱን በሊዝ ለ99 ዓመት የያዝነዉ በመሆኑ እና ያቀረብነዉም ክስ የባለቤትነት ለማስመለስ በመሆኑ በሰ/መ/ቁጥር 43600 ላይ በተሰጠዉ የሕግ ትርጉም መሰረት ክሱ በይርጋ የሚታገድ አይደለም፡፡ክሱ በይርጋ ሊታገድ የሚችል ነዉ ቢባል እንኳን ጊዜ መቆጠር ያለበት ተጠሪ ይዞታችንን በሕገ-ወጥ መንገድ አስፋፍተዉ ከያዙበት ከ2009ዓ/ም ጀምሮ ሊሆን ሲገባ ተጠሪ ከ1998ዓ/ም ጀምሮ መሬቱን ይገፍዋለሁ በማለት ባልተከራከሩበት ከዚህ አንጻር በማስረጃ ተጣርቶ እንዲወሰን በክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት ጉዳዩ ለወረዳ ፍርድ ቤት እንዲመለስ የተሰጠዉ ዉሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት ስለሆነ ይታረመልን በማለት በመጠየቅ ነዉ፡፡

ሰበር አጣሪ ችሎት አቤቱታዉን መርምሮ ጉዳዩ አስቀድሞ በሰ/መ/ቁጥር 43600 እና 210477 ላይ ከተሰጠዉ አስገዳጅ የሕግ ትርጉም እንዲሁም በፍ/ብ/ሕግ ቁጥር 1677/2 እና 1845 ስር ከተደነገገዉ አንጻር እንዲመረመር ለሰበር ሰሚ ችሎት አስተላልፏል፡፡

ከዚህ በላይ አጠር ባለ መልኩ የተመለከተዉ ግራ ቀኝ በክልሉ ፍርድ ቤቶች ያቀረቡትን ክርክርና አስቀድሞ በዚህ ችሎትና በክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት የተሰጡ ዉሳኔዎች የሚመለከከት ሲሆን የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት ክሱ በፍ/ብ/ሕግ ቁጥር 1845 መሰረት በአስር ዓመት ይርጋ ሊታገድ የሚችል እንደሆነ ገልጾ የወረዳዉ ፍርድ ቤት የይርጋ ጊዜዉ የሚቆጠርበትን ጊዜ አጣርቶ ክሱ በይርጋ ጊዜ ቀሪ መሆን አለመሆኑን አጣርቶ እንዲወስን ጉዳዩን በመመለሱ የተፈጸመ መሰረታዊ የሕግ ስህተት መኖር አለመኖሩን አግባብነት ካለዉ ሕግ ጋር በማገናዘብ እንደሚከተለዉ መርምረናል፡፡

እንደመረመርነውም በልዩ ሕግ በተለየ ሁኔታ ካልተደነገገ በስተቀር እንዲህ አይነት የፍትሐ ብሔር ክርክር መመራትና እልባት ማግኘት ያለበት በፍትሐ ብሔር ሥነ ሥርዓት ሕጉ በተዘረጋዉ ሥርዓት መሰረት

ማስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ

ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም !

ነዉ፡፡ በዚህ መልኩ በፍትሐ ብሔር ሥነ ሥርዓት ሕጉ የክርክር አመራር የተዘረጋበት ምክንያት በማስረጃ ሊረጋገጥ የሚችል የፍሬ ነገር ክርክር እና በሕግ ላይ ተመስርቶ ዉሳኔ ሊሰጥበት የሚገባ ነጥብ ጉዳዩን በሚዳኘዉ ፍርድ ቤት ተረጋግጦ ለክርክሮች ምክንያታዊ በሆነ አጭር ጊዜ እና በዉስን የሰዉና የገንዘብ ሀብት ተገቢዉን እልባት መስጠት እንዲቻል ነዉ፡፡በዚህ አግባብ የፍትሐ ብሔር ጉዳይ የቀረበለት ፍርድ ቤት የክርክሩን ሥረ ነገር፣የክስ ምክንያት፣በተከራካሪ ወገኖች የቀረበዉን ክርክር እና ማስረጃ ከግምት ዉስጥ ያስገባ ትክክለኛ የሕግ እና የፍሬ ነገር ጭብጥ በመያዝ ጉዳዩን የመምራት ፣በተጠየቀዉ ዳኝነት እና በአከራከረዉ ጭብጥ ላይ ተገድቦ ዉሳኔ የመስጠት ኃላፊነቱን በአግባቡ ተግባራዊ ሳያደርግ ክርክሩን የሚመራ ከሆነ ክርክሩ ከጊዜ ፣ከሰዉ ሀብት እና ከወጪ አንፃር ዉጤታማ እንዳይሆን በማድረግ ፍትህ የሚያጓድል ድምዳሜ ላይ የሚያደርስ ስለሚሆን የሥነ ሥርዓት ሕጉ የቆመለት ዓላማ እንዳይሳካ በማድረግ የተከራካሪ ወገኖችን የስረ ነገር መብት (substantive right) እስከማሳጣት የሚደርስ ጉዳት ያስከትላል፡፡ ስለሆነም በሥነ ሥርዓት ሕጉ የተዘረጋዉን የክርክር አመራር ሂደት ተከትሎ ለክርክሮች ተገቢዉን እልባት መስጠት ይገባል፡፡

ከላይ የተመለከተዉን ዓላማ ለማሳካትት የፍትሐ ብሔር ሥነ ሥርዓት ሕጉ ከዘረጋቸዉ ሥነ ሥርዓታዊ ደንቦች አንዱ የይግባኝ አቀራረብ እና ይግባኝ ማቅረቢያ ጊዜ ነዉ ተብሎ በሕጉ የተደነገገዉ ሥነ ሥርዓታዊ ደንብ ነዉ፡፡ ይኸዉም በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 320(3 እና 4) ጣምራ ንባብ መሰረት ማንም ሰዉ እንዲታሰር ወይም በማረፊያ ቤት ተይዞ እንዲቆይ የተሰጠ ትእዛዝ ካልሆነ በስተቀር እንዲሁም ከሥረ ነገሩ ፍርድ በፊት አንድ ተከራካሪ ወገን በእጁ ያለዉን ንብረት ለሌላዉ ወገን እንዲያዘዉር የተሰጠ ዉሳኔ ካልሆነ በስተቀር በሥረ ነገሩ ላይ የመጨረሻ ፍርድ ከመሰጠቱ በፊት በመጀመሪያ ደረጃ በሚቀርብ መቃወሚያ ላይ በሚሰጥ ዉሳኔ ላይ ብቻ ይግባኝ ማቅረብ እንደማይቻል የተደነገገዉ ደንብ ነዉ፡፡

እንዲሁም በኢፌዲሪ ሕገ መንግሥት አንቀጽ 80(3/ሀ) እና በፌዴራል ፍርድ ቤቶች አዋጅ ቁጥር 1234/2013 አንቀጽ 2(4/ሀ፣ለ እና ሸ)፣10(1/ሐ እና መ) መሰረት በክልል ጉዳይ ላይ በተሰጠ ዉሳኔ ላይ መሰረታዊ የሕግ ስህተት ተፈጽሟል በሚል የሰበር አቤቱታ ለፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ሊቀርብ የሚችለዉ በዚሁ አዋጅ አንቀጽ 2/5 ስር እንደተመለከተዉ በጉዳዩ ላይ የመጨረሻ ዉሳኔ ከተሰጠበት ብቻ ነዉ፡፡በኢፌዲሪ ሕገ መንግሥት አንቀጽ 80(3/ለ) እና በ1994ዓ/ም ተሻሽሎ በወጣዉ በኦሮሚያ ብሔራዊ ክልል ሕገ መንግሥት አንቀጽ 67(2/ሐ) ስር እንደተመለከተዉ በክልል ጉዳዮች ላይ በክልሉ ፍርድ ቤቶች በተሰጠ የመጨረሻ ዉሳኔ ላይ መሰረታዊ የሕግ ስህተት ተፈጽሟል በሚል የሚቀርብ አቤቱታ የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ተቀብሎ በሰበር ችሎት የማየትና የማረም ሥልጣን ተሰጥቶታል፡፡ በመሆኑም በክልል ጉዳይ ላይ የተሰጠ የመጨረሻ ዉሳኔ በአዋጅ ቁጥር 1234/2013 አንቀጽ 2(4/ሀ፣ለ እና ሸ) እና 10(1/ሐ እና መ) መሰረት መሰረታዊ የሕግ ስህተት ተፈጽሟል በሚል የሚቀርብ የሰበር አቤቱታ

ማስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ

ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም !

ይህ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት በሰበር ሰሚ ችሎት መመርመር የሚችለዉ አስቀድሞ በክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት በጉዳዩ ላይ የመጨረሻ ዉሳኔ ሲሰጥበት ብቻ ነዉ፡፡

በያዝነዉ ጉዳይ ከላይ አጠር ተደርጎ እንደተገለጸዉ ለክርክሩ መነሻ የሆነዉ ጉዳይ ከሕግ አግባብ ዉጭ ተጠሪ ከይዞታቸዉ ጋር ቀላቅለዉ ይዘዋል የተባለዉን የከተማ መሬት አስለቅቆ ለመረከብ ዳኝነት በመጠየቅ የቀረበ ክስ የሚመለከት ነዉ፡፡ ተጠሪ ደግሞ ክሱ በይርጋ ቀሪ የሆነ ነዉ በማለት የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ በማቅረብ ተከራክረዋል፡፡ክሱ በይርጋ ቀሪ የሆነ ነዉ የሚል መቃወሚያ ሲቀርብ የይርጋ ጊዜዉ ሊቆጠር የሚገባበት ጊዜ አጣርቶ እና ለጉዳዩ ተፈጻሚ የሚሆነዉን የይርጋ ጊዜ የሚደነግግ የሕግ ድንጋጌ ለይቶ ዉሳኔ የመስጠት ኃላፊነት የፍርድ ቤቶች ነዉ፡፡ጉዳዩን በመጀመሪያ ደረጃ ዳኝነት ሥልጣን ተቀብሎ ዉሳኔ የሰጠዉም ሆነ አሁን ላይ በክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት ጉዳዩ እንደገና ተጣርቶ በይርጋ መከራከሪያ ላይ ዉሳኔ እንዲሰጥ የተመለሰለት በኦሮሚያ ክልል ለአዳማ ወረዳ ፍርድ ቤት ነዉ፡፡ በመሆኑም ክስ የቀረበበት ጉዳይ የክልል ጉዳይ መሆኑ አከራካሪ አይደለም፡፡

የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት አስቀድሞ ግራ ቀኙን አከራክሮ በመ/ቁጥር 221409 በቀን 28/03/2015 ዓ/ም በሰጠዉ ዉሳኔ የስር ፍርድ ቤቶች የአመልካቾች ክስ በፍ/ብ/ሕግ ቁጥር 1845 መሰረት በአስር ዓመት ይርጋ ጊዜ ቀሪ ሆኗል በሚል በሰጡት ዉሳኔ ላይ መሰረታዊ የሕግ ስህተት መፈጸም አለመፈጸሙን የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት መርምሮ እንዲወስን ጉዳዩን መመለሱን ከክርክሩ ተገንዝበናል፡፡ይህንን ተከትሎ የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት ከላይ እንደተመለከተዉ የአመልካቾች ክስ በፍ/ብ/ሕግ ቁጥር 1845 መሰረት በይርጋ ሊታገድ የሚችል ነዉ የሚል ድምዳሜ ላይ ቢደርስም የይርጋ ጊዜዉ መቆጠር ያለበት ከ1998ዓ/ም ጀምሮ ነዉ ወይስ በ2010ዓ/ም ጀምሮ የሚለዉን የወረዳዉ ፍርድ ቤት በማስረጃ አጣርቶ የአመልካቾች ክስ በይርጋ የታገደ መሆን አለመሆኑን በተመለከተ ዉሳኔ እንዲሰጥ ጉዳዩን ለወረዳ ፍርድ ቤት መልሷል እንጂ የአመልካቾች ክስ በይርጋ ቀሪ የሆነ ነዉ የሚል ድምዳሜ ላይ ባለመድረሱ የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት በጉዳዩ ላይ የመጨረሻ ዉሳኔ አልሰጠም፡፡የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት ተፈጻሚነት ያለዉ የሕግ ድንጋጌ ነዉ ብሎ የሚያነዉን መለየቱ በጉዳዩ ላይ የመጨረሻ ዉሳኔ እንደተሰጠ የሚቆጠር አይደለም፡፡

ሲጠቃለል ምንም እንኳን የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት የአመልካቾች ክስ በፍ/ብ/ሕግ ቁጥር 1677/2 ስር በተደነገገዉ መሰረት በፍ/ብ/ሕግ ቁጥር 1845 መሰረት በአስር ዓመት ይርጋ ሊታገድ የሚችል ነዉ የሚል ድምዳሜ ላይ የደረሰ ቢሆንም ገና የአመልካቾች ክስ በይርጋ ቀሪ ሆኗል ተብሎ አልተወሰነም፡፡አመልከቾች ያቀረቡት የከተማ ቦታ ባለይዞታነት መብት የመፋለም ክስ በፍ/ብ/ሕግ ቁጥር 1677/2 እና 1845 መሰረት በአስር ዓመት ይርጋ ቀሪ የሚሆን ነዉ? ወይስ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በሰ/መ/ቁጥር 43600 እና 210477 ላይ በሰጠዉ የሕግ ትርጉም መሰረት በይርጋ ሊታገድ የማይችል ነዉ? በሚለዉ ጭብጥ ላይ በዚህ ሰበር ሰሚ ችሎት ዉሳኔ መስጠት የሚቻለዉ አስቀድሞ የአመልካቾች ክስ በይርጋ ቀሪ ሆኗል ወይም አልሆነም? በሚለዉ መሰረታዊ ጭብጥ ላይ ዉሳኔ ከተሰጠ በኋላ በዉሳኔዉ ላይ

ማስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ

ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም !

ሥርዓቱን ጠበቆ ጉዳዩ በየደረጃዉ ባሉት የክልሉ ፍርድ ቤቶች ታይቶ የመጨረሻ ዉሳኔ ከተሰጠ በኂላ ጉዳዩ ለዚህ ሰበር ሰሚ ችሎት ሲቀርብ ነዉ፡፡በመሆኑም የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት ለጉዳዩ ተፈጻሚነት ያለዉ በፍ/ብ/ሕግ ቁጥር 1845 ስር የተደነገገዉ የአስር ዓመት የይርጋ ጊዜ ነዉ በማለት የደረሰበት ድምዳሜ የአመልካቾች ክስ የማቀርብ መብት በይርጋ የታገደ ነዉ ተብሎ እንደተወሰነ የመጨረሻ ዉሳኔ የሚቆጠር ባለመሆኑ አመልካቾች ያቀረቡት የሰበር አቤቱታ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 320/3 ፣በፌዴራል ፍርድ ቤቶች አዋጅ ቁጥር 1234/2013 አንቀጽ 2/5 እና በኢፌዲሪ ሕገ መንግሥት አንቀጽ 80(3/ሀ) መሰረት ለዚህ ሰበር ሰሚ ችሎት ቀርቦ ለመታየት ብቁ አይደለም በማለት የሰበር አቤቱታዉን አልተቀበልንም፡፡

## <u>ት ዕ ዛ ዝ</u>

የዉሳኔዉ ግልባጭ ለግራ ቀኙ ይሰጣቸዉ፡፡ መዝገቡ ተዘግቷል፤ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ  የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ፅ/ወ

<u>ማስታወሻ</u>፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ

ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም !